# ይ ቻ ላ ል !

**መቻል አለበት!** **መቻል ይኖርበታል!**

# YICHALAL!

*ይቻላል ቅጽ ፩፣ ቁጥር ፪፣ ሰኔ ፪ሽህ ፩ ዓ/ም.* *Yichalal Vol. 1; Issue No. 2 June, 2009*

**በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት የሕዝብ ግንኙነትና ማስታዎቂያ ክፍል በየወሩ የሚወጣ ልሳን**



UEDF, P.O.Box 73796* Washington D.C.20056-3796; hebret.org; E-mail: uedf.hebret@yahoo.com


## ርዕሰ-አንቀጽ፡

**እውን ሕዝብ የሚበጀውንና የሚሻውን ሣይሆን የሚገባውን መንግሥት ነው የሚያገኘው?**
**ምንስ ዓይነት ተቃዋሚ፣ - የአገርና የሕዝብ ዘለቄታዊ ጥቅሞች ላይ የሚያተኩርና ሕዝብ አምኖ የሚከተለው ወይስ ሕዝብ መስማት የሚፈልገውን የሚስተጋባና የሚከተል?**

ለአገራችን ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ የተሻለ ሥርዓትን ለማስገኘት በቅንነትና በቁርጠኝነት የታገሉና ክቡር መስዋዕትነትን የከፈሉ፣ አሁንም በመክፈል ላይ የሚገኙ ዜጎች ብዙ ናቸው፡፡ ሆኖም ግን ለፍትኅ፣ ለእኩልነትና ለአገር አንድነት የተከፈለውን መራር መስዋዕትነትና እነኝህ ታጋዮች ያነገቡትን በጎ ራዕይ የሚመጥን ውጤት አለመገኘቱ አሌ የሚባል አይደለም፡፡
ማንኛውም ሕዝብ የሚያገኘው የሚሻውንና የሚፈልገውን መንግሥት ሣይሆን የሚገባውን ነው የሚል ብሂል በተደጋጋሚ መሰማቱ አዲስ ነገር አይደለም፡፡



ይኽ አባባል የሚገልፀውን በጥሬው ስናስቀምጠው ሕዝብ በአንድ መልኩ ይሁን በሌላ ካልፈቀደ ወይም ዝምታን ካልመረጠ በስተቀር በላዩ ላይ የሚጨፍርና እረግጦና ጨቁኖ የሚገዛው ቀርቶ በራሱ ላይ ማንም ከፍላጎቱ ውጭ የሚሄድና የሚሠራ መንግሥት ሊኖረው አይችልም ማለት ይሆናል፡፡ በዚኽ ብሂል እንግዲህ የጀርመን ሕዝብም የናዚ አረመኔዎች፣ የጣልያን ሕዝብም ፋሽስቶች፣ የኢትዮጵያ ሕዝብም ቀደም ሲል ደርግ አሁን ደግሞ የሕወሓት/ ኢሕአዴግ ጎሰኛና ጠባብ አሸባሪዎች በላዩ ላይ በመንግሥትነት ጉብ ቢሉበትና ቢጨቁኑት፣ ቢረግጡት፣ ቢያንገላቱት፣ ቢያስሩት ቢገድሉት፣ ቢያሰድዱት፣ ቢያምሱት፣ እንዳሻቸው ቁም-ስቅሉን ቢያሳዩት ይገባዋል እነሱንና የጭቆና አገዛዛቸውን መሸከም የሚችል ትከሻ ስላለው ወይም አሜን ብሎና ፈቅዶ ያደረገው ስለሆነ ይገባዋል የሚል ለገዥዎች ኃጢአት፣ አረመኔአዊና ኢ-ሰብዓዊ አድራጎትና ወንጀል ሁሉ ተጠያቂነትን በራሱ በሕዝቡ ላይ የጣለ ደፈናዊ ብይን ሆኖ እናገኘዋለን፡፡
ምንም እንኳን ኢትዮጵያውያን በፈርኀ-እግዚአብሔር መንፈስም ይሁን ተሿሚና

ባለሥልጣንን ከማክበር ልማድ የተነሣ የሚደርስበትን ግፍና በደል በትዕግሥት የመቀበል አዝማሚያዎች ያሳየ ሕዝብ ቢሆንም፤ መከራው ሲበዛና የግፉ ቋት ሲሞላ፣ በተለይም በክብር-በኩራቱና በሱነቱ ላይ ሲመጣበት እምቢኝ አሻፈረኝ ብሎ ግፍና ጭቆናን መታገሉ አሌ የማይባል ጉዳይ ነው። ይኽ እምቢተኝነትና አልገዛም ባይነት በግለስብ ከሚደረግ አመፃ እስከ ሕዝብ መነሳሳት ድረስ በልዩ ልዩ የአገሪቱ ሕዝብ ዘንድ ተንፀባርቋል። ጣልያን ከአገራችን ተሸንፎ እንደተባረረ በትግራይ፣ ከዚያም በጎጃምና በባሌ፣ ወዘተ… የተደረጉት ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች ብሶት ላይ የተመሠረቱና ይኽንን እምቢተኝነት ያንፀባረቁ ሃቆች ነበሩ። በደርጉም ጊዜ በርካታ የኅብረተሰብ ክፍሎችና በልዩ ልዩ የአገሩ አካባቢዎች መሣሪያ እስከማንሣት የደረሱ ሕዝባዊ አመፃዎች ተካሂደዋል። በደርግ የአሥራ-ሰባት ዓመታት ብልሹ አገዛዝ የተደቆሰው፣ መከራውን ያየውና ጦርነት እጅ እጅ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ምንም እንኳ ሕወሓት/ኢሕአዴግ በአገር አንድነትና የሕዝብ መብቶች መከበር ላይ ጥርጣሬው ቢኖረውም (ቢያንስ ሙሉ እምነት እንዳልነበረው ግልፅ ነው) ለደርግ የተነሥ ጥሪ ትብብር በመንፈግ በር ከፍቶ ለሥልጣን አብቅቷቸዋል።

ሕወሓት/ኢሕአዴግ ይኽንን ኀሉፋዊ የሕዝብ ድጋፍ (passive support) ተጠቅሞ በሥልጣን ለመቆየት የሚችለው ሕዝብ ለጋራ ብሶቱና መፃዒ ዕድሉ በጋራ እንዳይቆም ማድረግ ሲችል እንደሆነ በማሰብ ሕዝቡን ቋንቋን መሠረት ባደረገ አፈረጃጀት ከፋፈለው። ይኽም የከፋፍለህ ግዛ ዘይቤ በሥራ ላይ ለአሥራ-አራት ዓመታት በሥራ ላይ ከዋለና በገዥዎቹ እምነት ክፍፍሉ በማይቀለበስበት ደረጃ መሠረት እንደያዘ ከተማመኑ በኋላ ምርጫ ዘጠና-ሰባት የኢትዮጵያ ሕዝብ ለጋራ ዕድሉ እንደ አንድ አገር ሕዝብ እንደሚያስብና መብቶቹን አስከብሮ በአንድነቱ መኖርን እንደሚፈልግ የአንድነት ኃይሉን በመምረጥ ያለውን አርቆ-አስተዋይነት፣ ብስለትና ቁርጠኝነት በማያወላዳ መልክ በማረጋገጥ የከፋፋዮችን ከይሲ ጥረት እንደሻረውና ያደረጉትም ድካም ከንቱ እንደሆነ አሳይቷል።

በርግጥ ሕዝብ አስከፊ ሥርዓቶችን ወድዶ እንደማይቀበል የታወቀ ነው። ሆኖም በማንኛውም ጊዜ አንድ አናሣ የሆነ ከይሲ ቡድን በልዩ ልዩ ምክንያቶች፣ ሰበቦችና አጋጣሚዎች ሥልጣን ላይ ከተቆናጠጠ በኋላ ብዙኀኑን ሕዝብ አብሮ እንዳይቆም በልዩ ልዩ መንገድ መበተንና አሸብሮ መግዛት ስለቻለ ሕዝብ የሚገባውን መንግሥት ነው ያገኘው ብሎ ለሰቆቃው ሕዝቡን ተጠያቂ በማድረግ በሕዝብ መፍረድ ትክክል አይመስለንም። በዚኽ ስሌት የሚራብ ሕዝብም ጥፋቱ የራሱ ነው ማለት ይሆናል።

ማንኛውም ሕዝብ የሚገባውን መንግሥት ነው የሚያገኘው የሚለውን አባባል በጥሬው በመውሰድ በንዴትም ይሁን በቁጭት ነገሮችን በቅጡ ባለማየት አንዳንዶች የኢትዮጵያ ሕዝብ እየወረደበት ያለውን ሰቆቃ እንደዚኽ ወይም እንደዚያ አገር ሕዝብ ማስወገድ ያልቻለው ፈሪ ስለሆነ ነው የሚል ከእውነት የራቀ የድፍረት አባባል የሰነዘሩም አልታጡም።

ሕዝብ የሚገባውን መንግሥት ነው የሚያገኘው የሚል ደፈናዊ ብይን ከመስጠት በፊት ግን የግፈኞቹን አደረጃጀትና አሠራር፣ በአምባ-ገነኖች የግፍ መዳፍ ሥር ተቀፍድዶ የተያዘው ሕዝብ ለዚያ ዓይነት መከራ ያበቁትን የውስጥና የውጭ ሁኔታዎች በቅጡ ለመረዳት መሞከሩ ተገቢ ይሆናል። ሕዝብ በቃኝ እንዲልና አሸብረውና ረግጠው የሚገዙትን ጨቋኞችና ግፈኞች ከራሱ ላይ አውርዶ እንዲጥል በቅድሚያ የጋራ ዕድሉን በጋራ መወሰን ቁልፍ በመሆኑ ከግለሰብ ጀምሮ ከአስተሳሰብ እስከተግባር እንደ አንድ ሕዝብ አንድ ላይ እንዳይቆም ደንቃራና እንቅፋት የሆኑበትን ሁሉ ማስወገድ ይኖርበታል። በጋምቤላ ይሁን በኦጋዴን፣ በትግራይ ይሁን በአርሲ፣ በአፋር ይሁን በከፋ፣ በላስታ ይሁን በወልቃይት፣ ወዘተ… በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል የሚኖር ዜጋ

ላይ በተናጠልና በተራ የሚደርስ ግፍና በደል፣ የመብት ጥሰትና ችግር የሁሉም የአገሪቱ ዜጎች ላይ የደረሰና የተፈጸመ ተደርጎ ካልተወሰደ፣ የግፈኞች ዕድሜ እንደሚራዘምና ግፉ እንደቀጥል ብቻ ሣይሆን እየባሰ እንዲሄድ፣ ኅብረተሰቡም በተስፋ መቁረጥ ቁራኛ ተጠምዶ ይበልጡን አምባ-ገነኖች የሽብር ሥርዓታቸውን በራሱ ላይ እንዲያደላድሉ ሁነታዎችን ማመቻቸት እንደሚሆን ይገነዘቧል።

በሥልጣን ላይ ያለም ይሁን ሥልጣን የሌለው ማንኛውም ክፍል ሕዝብን በልዩ ልዩ መንገድ፣ በጎሣ፣ በቋንቋ፣ በሐይማኖት፣ ወዘተ… የመለያየት ተግባር እስካለ ድረስ የአንድ አገር ሕዝብ ያለ ፍላጎቱና ይሁንታው እራሱ ላይ ቁጢጥ ብለው አሸብረውና አፍነው በሚያሰቃዩት ገዥዎች ላይ መነሣትና የጋራ ጥቅሙን በአስተማማኝ ሁኔታ ማስከበር የሚቻለው አይደለም። በመንግሥት ይሁን በተቃዋሚ ስም የሕዝብን አንድነት የሚሸረሽር አካሄድን መከተል የሕዝብ ሰቆቃ እንዲቀጥል አስተዋጽዖው ቀጥተኛና የማይታበል እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል።

ሕወሓት/ኢሕአዴግ ሕዝባችን ለጋራ ጥቅሙና ዕድሉ በጋራ እንዳይቆም የሚከተለውን መርኅ-ተግባር (ፖሊሲ) እና የሚፈጽመውን ሕዝብን የመከፋፈል ተግባር ሁሉ በአፍራሽነትና በአሉታዊነቱ ስንቃዎም በተቃዋሚው ጎራም በኩል ሕዝብ በአባ-ገነኖችና በጨቋኞች ላይ በጋራ እንዳይቆምና እንደ አንድ አገር ዜጋ የወደፊት ዕድሉን በጋራ እንዳይወስን በልዩ ልዩ መልክ ተለያይቶ እንዲቆም የሚደረግ ጥረትም ውጤቱ የአባ-ገነኖችን ዕድሜ ማራዘም ይሆናል።

ስለሆነም ሁሉንም የግፉ ሰለባ አድርጎ የያዘ የአምባ-ገነን አገዛዝ ዕድሜ እንዲያጥርና ለተሻለ የጋራ መፃዒ ዕድል እውን መሆን የመጀመሪያው ተግባር የሕዝብ አንድነትን ማረጋገጥ ይሆናል። ።

ሁለተኛ ሕዝብ በልዩ ልዩ ሰበቦችና ምክንያቶች ሳቢያ በመኻሉ የሚደረግ የመከፋፈል አባዜን ካስወገደ በኋላ እንደ አንድ ሕዝብ በጋራ እንዲቆም የሚያ-ደራጀው፣ ታግሎ የሚያታግለውና እግቡ ሊያደርሰው የሚችል የጠራ ራእይ ያለው ቁርጠኛ አመራር የሚሰጠው ድርጅት ያስፈልገዋል። እንግዲኽ ጥያቄው ያለው እዚኽ ላይ ነው። ሕዝባችን እንደ አንድ ሕዝብ በጋራ ቆሞ የአባ-ገነኖችን ሥርዓትና የችግር አዙሪቶችን በማያዳም መልኩ እንዲሰብር እና ሁለንተናዊ መብቶቹ የሚከበሩበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባለቤት እንዲሆን ከግላዊ፣ ቡድናዊና ድርጅታዊ ጠባብ አስተሳሰብና ምኞት ወጣ ብሎ በሕዝብና በአገር ደረጃ ለሕዝብና ለአገር ቅድሚያ የሰጠ አሰላለፍ ያስፈልጋል። ሕዝብ ብሶቱ ሲበዛበትና ምሬቱ ቅጥ ሲያጣበት የሚያሰማውን እሮሮና ቁጭት በመከተል ብቻ አካሄዱ፣ አፈጻጸሙና በተለይም ድምዳሜው በቅጡ ሳይጠና፣ በበቂና በተገቢም መጣኝ ውይይት፣ ምክክርና የአሳብ ፍጭት ሳይደረግበት ሕዝቡ ሊሰማ የሚፈልገውን በማሰብና ምኞትን ለማስተጋባት ብቻ ብድግ ብሎ "አዲስ" አቅጣጫ ለመያዝና አዲስ አሰላለፍ በተናጠል ለመከተል ማሰብ ተሳስቶ ሕዝብን ስሕተት ላይ መጣልን ሊያስከትል ይችላል የሚል ስጋት አለን። ሕዝብም ጊዚያዊ ብሶቱን በማየት በየጊዜው የሚከሰቱ አካሄዶችን ቆም ብሎ መመርመርና ጥብቅ ጥብቅ ጥያቄዎችን መጠየቅና በቂ ምላሽ ማግኘት ይኖርበታል። ይኽ ካልሆነ ሕዝብ የሚያገኘው የሚሻውንና የሚፈልገውን ሣይሆን የሚገባውን መንግሥት ነው እንደሚለው ብሂል፤ ቆም ብሎ ሳያሰላስሉ፣ ያለ ጠንካራና ግልፅ ማጠየቂያና ተሃስቦ የሚነገርን ብቻ እየተቀበሉ ድጋፍ መስጠት ወይም አያገባኝም ባወጣ ያውጣው ብሎ ተስፋ መቁረጥ፣ የሩቅ ታዛቢ ወይም ጨለምተኛ መሆን የዜግነት ኃላፊነትን መዘንጋትና የሚያስፈልገንንና ሊኖረን የሚችለውን ሣይሆን "የሚገባንን" ተቃዋሚ እንደምናገኝ ይገነዘቧል።

በኅብረቱ እምነት ለአገራችንና ለሕዝባችን የተሻለ የሕዝብ ይሁንታን የተላበሰ ሥርዓት ለማምጣት በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፍነው ወገኖች የምንከራከረው

ከአገዛዙ ከሚመነጩ አስተሳሰቦችና አካሄዶች ጋር ብቻ ሣይሆን ከማንም ይፍለቅ ከማን በአጠቃላይ የአገራችንን ደኅንነትና የሕዝባችንን ትሥሥር በተመለከተ የሚሰነዘሩ አስተሳሰቦችን ጭምር ነው፡፡ ኅብረታችን በግልፅ ውይይት ያምናል፡፡ በተለይም ለሕዝብና ለአገር በሕዝብና በአገር ስም እታገላለሁ የሚል ማንኛውም ክፍል ተጠያቂነት ስላለበት የሚሰነዘሩበትን እሱ ከያዘው የተለዩ አስተሳሰቦች በአስተሳሰብነታቸው ሊያያቸው የግድ ነው፡፡ የተለዩ አስተሳሰቦችን በተገቢ አለማስተናገድ ደግሞ የምንታገለው የአምባ-ገነኖች ባኅሪ እንጂ ለዴሞክራሲ እታገላለሁ የሚል ክፍል መሆን አይኖርበትም፡፡ በተለይም በተቃዋሚው ጎራ በተሰለፍነው ወገኖች መኻል ከሕዝብ የተደበቀ አጀንዳ የሌለበት፣ ግልፅና አቅጣጫ ያልሳቱ፣ የማያስቱና ገንቢ የአሳብ ፍጭቶች መኖራቸው ለምንታገልለት አሳብን ያለምንም ፍራቻ በነፃ ማንሸራሸር የሚቻልበት ያልታፈነና ግልፅ ኅብረተሰብ እውን መሆን በእጅጉ ይጠቅማል ብለን እናምናለን፡፡ ውይይቱም ሆነ ክርክሩ በግለሰብ ቀርቶ በድርጅት ላይ ሣይሆን በሚንፀባረቀው ወይም በተያዘው አስተሳሰብ ላይ መሆን ይኖርበታል፡፡ የምንታገለው አፋኝ ሥርዓት የተለየ አስተሳሰብን ማስተናገድ አለመቻሉ አንደኛው አሉታዊና የሚወገዝበት ገፅታው ነውና በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፍነው ክፍሎች የያዝነውና የምናራምደው አስተሳሰብ እንዲሁም የምንከተለው አዝማሚያ ላይ ጥያቄ አልፎም ነቀፌታ ቢነሣ ስህተትን መጠቆም ወይም ጉዳዩ ላይ የተሻለ ግልፅነት እንዲኖር ውይይት መጋበዝ እንደሆነ እንዲታወቅና ሕዝባችንም የጠራ አስተሳሰብና ተጠያቂነት ያለው አካሄድ ከሁላችንም እንደሚጠብቅና እንደሚገባው ተገቢ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል እንላለን፡፡

በመሆኑም 'ይቻላል' ለአገራችንና ለሕዝባችን ለምናካሂደው የፍትኅ፣ የእኩልነትና የአንድነት ሕዝባዊ ትግል አስተዋፅዖ የሚኖራቸውንና መርኅን የተከተሉ ከማንኛውም ወገን የሚቀርቡ ምጉራዊና ጥናታዊ ጽሑፎችን ለማስተናገድ ተዘጋጅታለች፡፡

በተቃዋሚው ጎራ በተሰለፍነው መኻል ግልጽና ይፋዊ ውይይትም ሆነ ክርክር አለመደረጉ ሁሉም የሚመስለውን ይዞ "አትድረሱብኝ" ዓይነት የተናጠል አካሄድን እንዲከተል እንዳደረገውና ይኸም እርስ በረስ መተራረምንም ሆነ የመቻቻል ፖለቲካን እንዳቀበ ግልፅ ነው፡፡ ይኸ ደግሞ አሁን ትግሉ ላይ ጉዳት እንዳደረሰና ይበልጥም ነገ እንዲኖር የምንፈልገው ግልፅነትና ተጠያቂነትን የተላበሰ የፖለቲካ ባህልን በመፍጠሩና በማዳበሩ ረገድ የሚኖረው ጫና ሊጤን ይገባል፡፡ ስህተትን መጠቆም የማይፈልግና የአሳብ ልዩነትን በቀና መንፈስ መቀበል የሚያቅተው እድገትንና የአስተሳሰብ ነፃነትን ምንነት ያልተረዳና እድገትን የሚፃረር ድፍን አእምሮ ብቻ ነው፡፡

በዚኽም መንፈስ በዚች የይቻላል እትም የኅብረቱ አመራር አባል ከሆኑት ከዶ/ር ነገደ ጎበዜ የመጀመሪያውን የግል አስተያየት እነሆ፡፡

በመተራረምና በግልፅ ውይይት ትግላችንን ወደተሻለ የጥራትና የእድገት ደረጃ እንውሰደው!

በጋራ ሕዝባዊ ትግል አስተማማኝ ድል!

እንበርታ!

ይቻላል! አዎን ይቻላል!! መቻልም ይኖርበታል!!!

--------- // --------

<u>ሐተታ፤</u> (*)

*(ይቻላል በዚኽ አምድ ሥር ኀብረቱ -ኢዴኃን - አቋሞቹን የሚያሳውቅበትና የሚያብራራበት፣ ከግለሰብ ምኁራን፣ ሙያተኞች፣ ተመራማሪዎችና የፖለቲካ ተንታኞች የሚቀርቡና ለፍትኅ፣ ለእኩልነትና ለአንድነት ለሚደረገው ቀጣይ ትግል የተሻለ ጥራትንና አቅጣጫን ሊሰጡ፣ ውይይትን ሊያጭሩና ሊጋብዙ ይችላሉ ብሎ ኀብረቱ ያመባቸውን ጽሑፎች ታቀርባለች።)*

የግል አስተያየት፣- በዶ/ር ነገደ ጎበዜ

## <u>የትግራይን ሕዝብ ለቀቅ፤ የሕወሓት/ኢሕአዴግን መሪዎች ጠበቅ!</u>

የብሔር ጥያቄን አስመልክቶ ከአሉት እውነታዎች እየተነሣን አንድ የጋራ የሆነ መደምደሚያ ላይ መድረስ አቃተን እንጂ ዛሬ በአገራችን ማንም አሌ ሊላቸው የማይችል ግልጽ የሆኑና በተጨባጭ አሃዞች ላይ ተመርኩዘው ሊደረደሩ የሚችሉ ሃቆች አሉ። በአሁኑ ጊዜ በአገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በይፋ አንድን ብሔር እወክላለሁ እያለ የሚቀጥፍ በዚኽ ብሔር ስም የተደራጀ አክራሪ ቡድን የአገሪቱን ማዕከላዊ መንግሥት፣ የጦር፣ የፖሊስ፣ የፀጥታ ተቋማትና የኤኮኖሚ እንቅስቃሴዋን በሙሉ ቁጥጥሩ ሥር ያደረገበት ሁኔታ ውስጥ ነን። በአገራችን ታሪክ አሁንም ለመጀመሪያ ጊዜ ሕዝባችን ይኽ የተጫነበት ሥርዓት "በአንድ ብሔር ለአንድ ብሔር" የተዋቀረ ሥርዓት ነው ብሎ እንዲያምን በግልጽ እየተገፋ ያለበት ሁኔታ ውስጥ እንገኛለን። አሁንም በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ እፍኝ የማይሞሉ የአክራሪዎች ጥርቅም በሕዝብ ላይ ለሚፈጽመው ወንጀል እንዳለ አንድን ብሔር የዚኽ ወንጀል አባሪ ተባባሪ አድርጎ ለማቅረብ ይኽ ነው የማይባል የስውርና የይፋ ሥነ-ልቡናዊና የፖለቲክ ጦርነት ሲያካሂድ እየታዘብን ነው።

የ'ግንቦት ሰባት' ንቅናቄ በቅርቡ ይፋ ያደረገው በኢትዮጵያ ሠራዊት ውስጥ የትግራይ ተወላጆች የማያወላዳ የበላይነት ቦታ መያዛቸውን የሚያሳይና ብዙ በማነጋገር ላይ ያለ አንድ ሰነድ ከነዚኽ ተጨባጭ ሃቆች በመጀመሪያ የጠቀስኩትን ማለትም "አንድን ብሔር እወክላለሁ እያለ የሚቀጥፍ" የአክራሪዎች ቡድን አገራችንን እየተቆጣጠረ መሆኑን በተጨባጭ መረጃ የሚያረጋግጥ ነው። ይኽም ሆኖ የዚኽ ሰነድ ይዘት ከፍተኛ የመረጃ ስብስብ ጥረት ተደርጎ፣ ከፍተኛ ምርምርና ጥናት ጠይቆ "የተደረሰበት" ምስጢር አይደለም። ከላይ የጠቀስኳቸውን ሁለት ሌላ የጥፋት አጀንዳቸውን ለማራመድ ሲሉ የሕወሓት መሪዎች ራሳቸው ሆን ብለው ለንባብ እንዲበቁ ወይም ወደ ሕዝብ ጆሮ እንዲደርሱ ከሚያደርጓቸው ስታቲስቲኮች የተለየ ወይም በነሱ ላይ የሚጨምር አንዳችም አዲስ ግኝት የለውም። ይኽንን እውነታ እኛ ለቀባሪ ለማርዳት በሚግደረደር ሰነድ ይፋ እናድርግ ስንል አክራሪዎቹም ለራሳቸው ፀረ-ሕዝብ ስትራቴጂ እንደሚያራግቡት ጠንቅቀን የምናውቀው ነገር ነው።

ከአንድ ከአሥራ-አራት ዓመታት በፊት (ጁን 1995) የኢሕአዴግ መንግሥት ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ አየር ኃይል አብራሪዎችን (ፓይለቶችን) ሲመርቅ ምሩቃኑ በሙሉ የትግራይ ተወላጆች <u>ብቻ</u> እንደሆኑ በራሳቸው በወቅቱ የአየር ኃይል አዛዥ በነበሩት በጄኔራል አበበ ተክለ-ሐይማኖት ሲገለጽ፣ በነዚሁ ዓመታት የኢንቬስትመንት ባለሥልጣን የተባለው ተቋም በየዓመቱ ኢንቬስትመንትን አስመልክቶ በሚያቀርባቸው ስታትስቲኮች በይፋ ለትግራይ ክልል የሚያደሉ እንደሆኑ ሲጠቁም ያኔም እንደ አሁኑ "የአንድ አናሣ ብሔር የጭቆና አገዛዝ" ተብሎ ብዙ ሲተችና ሲፃፍ ትዝ ይለኛል። በዚያን ወቅት እስቲ ከዚኽ ዘለቅ ብለን እንመልከት በሚል መንፈስ በየስብሰባው እላቸው ከነበሩትና በጽሁፍም ካሰፍርኳቸው አንዳንድ ነጥቦች መኻከል ዛሬም ቢሆን ከዚኽ የተለየ ብዙም ትንተና

የለኝምና አንዱን ጽሑፍ በሰፊው ልጥቀሰው::

"የሕወሓት ፕሮፓጋንዳ ዓላማ የትግራይ ሕዝብም ሆነ ሌሎች ብሔሮች በመተከል ላይ ያለው በብሔር የተማከለ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ 'በትግራይ ተወላጆች ለትግራይ ተወላጆች' የተተከለ አገዛዝ ነው ብለው እንዲያምኑ የመገፋፋት ዓላማ ነው:: በዚኽም መሠረት እየተተከለ ላለው የትግራይ ተወላጆች ኦሊጋርሺ የሚደረገው አድልዖ ሆን ተብሎ ዓይን እንዲያወጣ ታስቦ በይፋ የሚደረግ አድልዖ ነው:: ሠራተኞችና ሌሎች ባለሙያዎች በጅምላ ከሥራ እየተባረሩ በትግራይ ተወላጆች ይተካሉ:: በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያሉት መገናኛ ብዙኃን በትግራይ ስለሚደረገው የልማትና የግንባታ እንቅስቃሴ፣ በሕወሓት አባላትና ደጋፊዎች ባለቤትነት ስለሚቋቋሙ ኩባያዎች ሪፖርት ሳያደርጉ የሚያልፉ ሣምንታት እምብዛም ናቸው::

"ራሳቸው የትግራይ ተወላጅ የሆኑት የአየር ኃይሉ አዛዥ ጀኔራል አበበ ተክለ-ሐይማኖት ለአንድ ለመንግሥት ቅርበት ያለው ጋዜጣ በሰጡት ቃለ-ምልልስ 'የመጀመሪያው የአየር ኃይል ፓይለቶች ምሩቃን በታሪክ አጋጣሚ በሙሉ ከአንድ ብሔረሰብ ብቻ ናቸው' ሲሉን፣ መንግሥታዊ የሆነው የኢንቬስትመንት ባለሥልጣን ከ1983 እስከ 1988 ዓ.ም. ባለው ወቅት በጠቅላላው በአገሪቱ ክልሎች የተደረገው ኢንቬስትመንት ቢደመር በትግራይ ከተደረገው ያነሰ ነው ሲለን፣ በዚሁ መንግሥታዊ ተቋም ይፋ የሚሆኑት ስታቲስቲኮች በነፍስ ወከፍ ኢንቬስትመንት የተለያዩ ክልሎች ድርሻ ተዘርዝሮ ሲቀርብ የትግራይ ድርሻ 601 ብር ሆኖ የኦሮሞ ክልል 50 ብር ሲደርሰውና የአማራው ክልል ደግሞ እዚህ ግቢ የማትባል 7 ብር ነበረች ስንባል ማንም ቢሆን ይኽንን ሁሉ እንደ ተራ ለከፋ (wanton act of provocation) አድርጎ መቁጠር የለበትም::

"ይኽ ሆን ተብሎ የተነደፈ ማኬቬሊያዊ መሠሪ ስትራቴጂ እንዲህ ዓይነቱ ቅስቀሳ ሊያስነሣ በሚችለው "ፀረ-ትግራይ ስሜት" በመጠቀም የትግራይ ሕዝብ ሕወሓትን የጥቅሙ ጠባቂ ብቻ ሣይሆን በጠቅላላው ከቀሩት የአገሪቱ ብሔሮች ቁጣ የሚጠብቀው ወይም የሚያድነው ብቸኛ ኃይል አድርጎ እንዲያቅፈው የሚጥር ስትራቴጂ ነው:: አክራሪዎቹ ይኽንን የሚያደርጉት የትግራይ ወገኖቻችንን አስገድደው እጣ-ፈንታቸውን ከእነሱ ጋር እንዲያይዙና አገሪቱን በቀጣይነት ለመግዛት 'ጠንካራ መሠረት' (solid base) ለመጣል እንደሆነ ግልጽ ነው::" ((ETHIOPIA: A TRAGEDY IN THE MAKING , ADDIS DIGEST No 18, JUNE 1997)

ይኽ የጥቂት አክራሪዎች የጥፋት ስትራቴጂ ገብቶን እሱን ለመዋጋት የሕዝብን ወንድማማችነት የሚያጎለብት ስትራቴጂ እስካልነደፍን ድረስ "አንድ ብሔር" ሠራዊቱን፣ ፖሊሱን፣ የመንግሥት መዋቅሩን፣ ኤኮኖሚውን መሉ በሙሉ ቁጥጥሩ ሥር አድርጓል የሚለው ቅስቀሳ በቀጥታ የሕወሓት መሪዎች መሰሪ አጀንዳቸውን ለማራመድ ለትግራይ ሕዝብም፣ ለቀሩት የኢትዮጵያ ብሔረሰቦችም ለማስተላለፍ የሚፈልጉትን መልዕክት ማስተጋባትና የነሱን የቤት ሥራ መሥራት ይሆናል:: ሰሞኑን እንደምታዘበው ደግሞ የነዚኽን የጥፋት ኃይሎች አጀንዳ የማራመዱ ጉዳይ ከዚኽም አልፎ እየሄደ ነው:: እንደሚታወቀው እስካሁን ድረስ የሕወሓት መሪዎች 'የትግራይ ሕዝብ ብቸኛ ተወካይ ነን' እያሉ እራሳቸውን ሲያሞካሹ እኛ ደግሞ ከራሳችሁና በጥቅም ከያዛችኋቸው የትግራይና የሌሎች ብሔረሰቦች ጥቂት ተጠቃሚዎች በስተቀር ማንንም የማትወክሉ ጥቂቶች ናችሁ እያልን ስንሞግታቸው ቆይተን ነበር:: አሁን የተያዘው አዝማሚያ ከዚኽ ጤናማ አካሄድ የወጣ ይመስላል:: በዚኽ ጉዳይ የግንቦት ሰባት ንቅናቄ መሪዎች ጁን 4 ቀን በእንግሊዝኛ ቋንቋ ባወጡት መግለጫ * "ዓለም-አቀፉ ኮሙኒቲ

ከሕዝቡ 6% ብቻ የሚወክለው ሕወሓት የሚከተለውን ፖሊሲ አስከፊ ገፅታ ጠጋ ብሎ እንዲመረምር ...” የሚል ጥሪ በማስተላለፍ እነዚኽን ጥቂቶችና የትግራይን ሕዝብ ሲያምታቱና ለነዚኽ ጥቂቶች የትግራይ ሕዝብ ብቸኛ ተወካይነት ሙሉ እውቅና ሲሰጣቸው እናያለን። (*Supporting Ethno-centric Policies is Complicity with Ethiopian Government Crimes Against Population. June 4, 2009)

እጅግ ግፈኛና ሙሰኛ የሆነ ጎብረ-ብሔር ገዥ መደብ እየተተከለ ባለበት አገር ይኽንን ችላ ብሎ እንዳለ አንድን ራሱ በጭቆና መዳፍ ሥር ያለን ሕዝብ ያለበትን ወደ “ገዥ ብሔርነት” ለማሸጋገር መሞከር አደገኛና አጉል አካሄድ ነው።

አደገኛ አካሄድ፤ ምክንያቱም ሕዝባችን ከስግብግብነታቸውና ከኪሣቸው መሙላት ሌላ አለን የሚሉት ብሔርም ሆነ ቆመንለታል የሚሉት ሕዝብ የሌላቸው፣ ጎብረ-ብሔር ገዥዎችን ወደ ጎን ትቶ ከድኅነትና ከጎስቋላ ኑሮ ለማላቀቅ በአንድነት መቆም የሚኖርባቸውን ሚሊዮኖች እርስ በርስ ሊያናክስ የሚችል አካሄድ በመሆኑ።

አጉል አካሄድ፤ ምክንያቱም የዚኽ ገዥ ተብየ ብሔር ሕዝብ ያለበትን የኤኮኖሚና የፖለቲካ ጎስቋላ ሁኔታ የሚክድ በመሆኑ። የትግራይ ሕዝብ በኑሮው ከትላንቱ ዛሬ የተመቸው በፖለቲካው መስክስ ከትላንቱ ዛሬ ይበልጥ መብቱ የተጠበቀለት ሕዝብ ነወይ? አይደለም።

የኢሕአዴግ መሪዎች አገራችን ዛሬ በዓመት ከአሥር በመቶ በላይ በእጥፍ አሃዝ እድገት እያስመዘገበች እንደሆነ ነጋ-ጠባ ይለፍፉልናል። ሆኖም የሚደረደሩት አሃዞች ምን ያልኽል እውነት ቢሆኑ እንኳን ተመዘገበ የሚባለው እድገት የአማራ፣ የኦሮሞ፣ የጉራጌ፣ ወዘተ.... እና ከነዚኽም ይበልጥ ደግሞ ጥቂት የትግራይ ልኁቃን የናጠጠ ሃብት የሚያካብቱበት፣ በአገራችን ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የሃብት መበላለጥ ጣራ የነካበት፣ በሙሰኙነት የተበከለ ለጥቂቶች የተበጀ ደም መጣጭ (predatory) እድገት እንጅ የአገር ልማት አይደለም። መቀሌና አድዋ የሚሠሩ ሰማይ-ጠቀስ ፎቆችን በቤዛነት እየጠቀሱ እነዚኽ ከተሞች እየለሙ የነዚኽ ከተሞች ኗሪ እየተመቸው ነው የሚሉ ሰዎች መኖራቸው አይቀርም። ለዚኽ መልሱ ቀላል ነው። አዲስ አበባ የሚደረገው የተጧጧፈ የፎቆች ግንባታ ይቺን ከተማችንን በኗሪዎቿ ጉስቁልና ከአፍሪቃ ተወዳዳሪ የሌላትና "The Slum Capital of Africa" ከሚል ስመ-ጥፉነት እንዳላዳናት፣ ሰማይ-ጠቀስ ፎቆች ጋር በጎስቋላ ጎጆዎች ሰማይ-ጠቀስ ድህነት የሚስፋፋባት፣ በዓለም ካሉ ዋና ከተሞች በጎስቋላነትና በቆሻሻነት ስድስተኛውን ቦታ ያስያዛት “እድገት” እንጂ ከዓመት ዓመት እየጨመረ ለሚሄደው ድሃና ጎዳና ተዳዳሪ ወገናችን መፍትኄ እንዳላመጣ ማስታወሱ ብቻ ይበቃል።

አዎን እድገት አለ። ግን ደግሞ እድገትና ልማት ለየቅል ናቸው። ዛሬ በአገራችን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ልማት ማለት ከሁሉም ከሁሉም በፊት የረሃብን መቅሰፍት አዙሪት ሰብሮ በሱ ላይ ከዓመት ዓመት የሚሊዮኖችን ኑሮ እያሻሻለ የሚጓዝ ሂደት ብቻ ነው። ይኽንን አዙሪት አልሰበርነውም። እዚኽ ላይ ነው በትግራይ “ልማት” እየተካሄደ ነው የሚሉን ወገኖች ስህተት። ረሃብ በአገራችን እየከፋ እንጂ እየጠፋ አልሄደም። የትግራይ ሕዝብ ደግሞ አማራው፣ ኦሮሞው፣ ወላይታው፣ ሲዳማው፣ ጋምቤላው፣ ወዘተ... እየተራበ እሱ ጠግቦ የሚያድር ሕዝብ አይደለም። “ስታቲስቲክሱ” የሚያሳየው ይኽ በንጉሡም በደርግም ዘመን 'ከተገቢ ድርሻው በላይ' ይራብ የነበረ መከረኛ ሕዝብ ከአሥራ-ስምንት ዓመታት በላይ በስሙ የሚነግደው የሕወሓት አገዛዝ በኋላም አስከፊ የሆነ የድህነትና የረሃብ አዙሪት ውስጥ የሚዳክር “በፐርሰንቴጅ”

ሲሰላ አሁንም ከድርሻው በላይ እየተራበ ያለ ሕዝብ እንደሆነ ነው። በዚኽ ጉዳይ ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ ሳያሰልሱ ከዓመት ዓመት ይወጡ የነበሩትን አሃዞች ወደ ጎን ትተን የእርዳታ ማስተባበሪያ ድርጅት በያዝነው ዓመት ለዓለም-አቀፉ ኅብረተሰብ ያቀረበውን የእህል እርዳታ ጥያቄ ብንመለከት የምንገነዘበው ይኽንኑ ነው።

በአለፈው ጥር ወር 2001 ዓ/ም. በቀረበው የእርዳታ ጥሪ በያዝነው ዓመት “አስቸኳይ የእህል እርዳታ” የሚያስፈልጋቸው ዜጎች ቁጥር 4,945,425 እንደሆነ ተገልጧል። ማነው የት የሚራበው? በሦስት ክልሎች ተወስነን ብንመለከት ከነዚኽ ውስጥ 995,095 ርሃብተኞች በአማራው ክልል፣ 683,839 በኦሮሞ ክልልና 674,304 ደግሞ በትግራይ ክልል እንደሚኖሩ እናያለን። ምንም እንኳ በፖለቲካ ስሌት እንዳሻው አወለጋግደው ይፋ ያደረጉት የመጨረሻው የሕዝብ ቆጠራ ውጤት እጅግ አወዛጋቢ ቢሆንም ከሱ ተነስተን በየክልሉ ይኖራል ከሚባለው ሕዝብ ስንት ከመቶው ረሃብተኛ እንደሆነ ብንመለከት “ገዥው ብሔር” ከድርሻው በላይ በረሃብ መቅሰፍት እየተገረፈ እንደሆነ እንገነዘባለን። በአማራው ክልል ይኖራል ከሚባለው 20,042,845 ሕዝብ 5% እና በኦሮሞ ክልል ከ26,878,482 ሕዝብ ደግሞ 3.5% ርሃብተኛ ሲሆን በትግራይ ከ4,526,644 ሕዝብ 15% ያኽሉ ርሃብተኛ እንደሆነ እናያለን።

ይኽ አፍጥጦና አግጥጦ ያለ ሃቅ በመሆኑ አሌ ሊባል ሳይቻል ሲቀር ሌላ የሚቀርበው “መከራከሪያ” ከጠቅላይ ሚኒስትሩ እስከ ክፍለ-ጦር አዛዡ፣ ከየሚኒስቴሮች መምሪያዎች እስከ ወህኒ ዘበኛው ያሉት መንግሥታዊ ተቋማት ውስጥ የትግራይ ተወላጆች ጎልቶ የሚታይ ቦታ በመያዛቸው ብቻ ይኽ ሕዝብ “በተወካዩ” በሕወሓት አማካይነት የፖለቲካ ሥልጣኑን ጠቅልሎ ይዟል የሚለው መከራከሪያ ነው። ለዚኽም “ከተጨባጩ” ስታቲስቲክስ በተጨማሪ እንደ ማስረጃ የሚሰነዘረው ትንታኔ የትግራይ ሕዝብ በዚኽ መልክ የፖለቲካው ሥልጣን ተቋዳሽ በመሆኑ እንደ ሌሎቹ ብሄሮች ሕዝብ “በፀረ-ወያኔው ትግል” የጎላ አስተዋጽዖ ሲያደርግ አይታይም የሚል ክርክር ነው። ይኽም በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች የተነሣ የአለውን ተጨባጭ ሁኔታ ሳያገናዝብ በጭፍንና በስሜታዊነት የሚሰነዘር የተሳሳተ ክርክር ነው።

አንደኛው በትግራይ ክልልና በቀሩት የኢትዮጵያ ክፍሎች ያለው የፖለቲካ ሁኔታ የተለያየ ነው። በአገራችን በተለይም ከግንቦት ቅልበሳ ወዲህ ከዚያ በፊት በፍንጭም ደረጃ ቢሆን የነበሩት መብቶች ደብዛቸው ጠፍቶ እየተተከለና እየተጠናከረ ያለው አሸባሪና የለየለት የፖሊስ መንግሥት (Police State) ነው። ልብ አልነው አላልነው የትግራይ ሕዝብ እንደኛ ዛሬ ሣይሆን ገና ሕወሓት አገራዊ ሥልጣን ከመያዙ በፊት ጀምሮ በለየለት “የፖሊስ ክልል” ብለን ልንጠራው በምንችለው የአንድ ፓርቲ (ቶታሊታሪያን) ሁለንተናዊና ደፈናዊ ቁጥጥርና አገዛዝ ሥር የወደቀ ሕዝብ ነው። ዛሬ እኛ (የቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ) የመደራጀት፣ የፕሬስ ወዘተ. ነፃነቶች ደብዛቸው ጠፋ እያልን ተቃውሞአችንን እናሰማለን። ሆኖም ያኔ ድሮ ከምርጫ 97 በፊት በቀረው የአገራችን ክፍል የፕረስ ነፃነት ፍንጭ በነበረበት ወቅት እንኳን በመላ የአገራችን ክፍሎች ይሰራጩ የነበሩት መጽሔቶችና ጋዜጦች በትግራይ ክልል እንዳልነበሩ የአደባባይ ምስጢር ነው። ግንቦት 97 ላይ እነ አቶ መለስ "Calculated Risk" ወሰድን ብለው በአገሪቱ መድብለ-ፓርቲ ምርጫ “ፈቅደናል” ሲሉ ለትግራይ ሕዝብ ግን ያም በዛብህ ተብሎ እነ አቶ መለስንና ባለቤታቸውን ጨምሮ የሕወሓት ዋና ዋና መሪዎች ከ38ቱ የምርጫ ወረዳዎች በአሥራ-ሁለቱ ማለትም በአንድ-ሦስተኛው ያኽል ሌሎች ተወዳዳሪዎች ሳይፈቅዱ ለብቻቸውና ከገዛ ጥላቸው ጋር “ተወዳድረው” “እያሸነፉ” ለፓርላማ

እንደበቁ አይተናል። ለማነፃፀር ያኽል

በአማራው ክፍል ደግሞ በጠቅላላው ካሉት 138 የምርጫ ወረዳዎች ብአዴን/ኢሕአዴግ ብቻውን ለምርጫ የቀረበው በሦስት ወረዳዎች ብቻ እንደሆነ እናያለን። የትግራይ ሕዝብ ለምን ለወሬ ነጋሪ እንኳን ከሕወሓት ተወዳዳሪዎች ውጭ አንድም ተቃዋሚ አልመረጠም የሚል ጥያቄ ይነሣ ይሆናል። ጥያቄውን በሌላ በጥያቄ "ለመመለስ" ልሞክር።

ነፃ ፕረስ፣ የመደራጀት መብት፣ ወዘተ... ደብዛቸው በጠፋበት አፈናና ሽብር ከትግራይ ክልል ዘልቆ መላ አገራችንን ባጥለቀለቀበት ሁኔታ አምና በተደረገው የወረዳ ምርጫ የመምረጥ መብት ካለው ሕዝብ 93% ድምፅ ሰጥቶ ከጠቅላላው ድምፅ ኢሕአዴግ 97% ድጋፍ አገኘ ተብሏል። ምርጫ ቦርዱ የተደረገው ምርጫ "ነፃና ርቱዓዊ" ነበር ብሎ ይፋ ባወጣው ውጤት ለአዲስ አበባ ምክር ቤት ከተመደቡት 138 መቀመጫዎች 137ቱን ኢሕአዴግ "አሸንፎ" አንዷት ወንበር ለአንድ ተባራሪ የቅንጅት አባል ወድቃለች። በዚሁ በአዲስ አበባ በተደረገው የቀበሌ አስተዳደር ደግሞ በጠቅላላው ምርጫ በተደረገባቸው ቀበሌዎች ያሉትን 2,970 መቀመጫዎች አንድም ሣይቀር ኢሕአዴግ በሙሉ አፋፍሷቸዋል ተብለናል። በደቡብ ሕዝቦች ክልል ለዞን ምክር ቤቶች ለውድድር የቀረቡትን 830 መቀመጫዎች አንድም ሳይቀር ደኢሕዴን/ኢሕአዴግ አሸንፏል ተብሏል። በየክልሎቹም ከዚኽ የተለየ ሥዕል የለም። ጥያቄው እንግዲህ ይኽ ሁሉ የሆነው በመላ አገሪቱ የዚኽ ድርጅት ደጋፊዎች ብቻ ለመመረጥ የበቁት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር-እስከ-ዳር በኢሕአዴግ ደጋፊነት ስለተሰለፈ ነው ወይ? የሚል ነው። መልሱ ግልፅ ይመስለኛል።

ሁለተኛ ማየት ያለብን ሌላ ቁም ነገር አለ። በዚኽ መልክ የመምረጥ ዕድል ተነፍጎትና ጭብርብርብም ተጨምሮበት የክልሉን 38 የፓርላማ መቀመጫዎች ለሕወሓት ለማስረከብ የተገደደው የትግራይ ሕዝብ ምርጫ ሲኖረውስ ይኽንን መብቱን እንዴት ተጠቀመበት? ለዚኽ ደግሞ ከዚኽ የአንድ ፓርቲ አገዛዝ ከተተከለበት ክልል ውጭ ያሉ የትግራይ ተወላጆች የማያወላዳ ዴሞክራሲያዊና ኢትዮጵያዊ መልሳቸውን ሰጥተዋል። እነዚኽ ወገኖቻችን ሌላው ቀርቶ በአዲስ አበባ ከተማ ሚዛን ሊደፉ በሚችሉባቸው አካባቢዎች እንኳን ለሕወሓት/ኢሕአዴግ ተወዳዳሪዎች ድንፃቸውን በመንፈጋቸው ለአዲስ አበባ አስተዳደር ለወሬ ነጋሪነት እንኳን አንድም "ወያኔ" ለመመረጥ ያልቻለበት ሁኔታ ነበር ግንቦት 97 የመሰከረው ሃቅ።

የትግራይ ሕዝብ "በፀረ-ወያኔው ትግል የጎላ ሚና አለመጫወት" የሚለውን በዚሁ መተው ይቻላል። በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ነገሩን "ጠበብ" በማድረግ የትግራይ ዴሞክራቶችና ልኂቃን በዚኽ ለዴሞክራሲ በሚደረግ ትግል የረባ አስተዋፅዖ ሲያደርጉ አይታይም የሚሉ አስተያየቶች ይሰነዘራሉ። ከትግራይ ሕዝብ አንፃር በብዛታቸው እዚኽ ግቡ የማይባሉ ቢሆኑም ዛሬ እየተተከለ ባለው የስድ ገበያ ኤኮኖሚ ግርግር ተጠቃሚ የሆኑ ቁጥራቸው የማይናቅ የትግራይ ተወላጅ የሆኑ ነጋዴዎች፣ ኢንቬስተሮች፣ ባለሙያዎች፣ የመንግሥት ባለሥልጣናትና በነሱ ዙሪያ የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች የሆኑ ወዳጆች፣ ዘመዶች እንዳሉ አሌ የማይባል ሃቅ ነው። እየተበጀ ያለው መረን የለቀቀ የሕዝብ ደም መጣጭ ሥርዓት አራማጆችና ተጠቃሚዎች ከየብሔሩ የተውጣጡ ቢሆኑም በዚኽ ሥርዓት ውስጥ የትግራይ ተወላጆች የአንበሣ ድርሻ እንዳላቸው ግልፅ ነው። በትግራይ ውስጥ ይኽ ደራሽ ኦሊጋርሺ(ኪ) ምንም ከሕወሓት ውጭ ያለ የግል ባለሃብት ሊንቀሳቀስ በማይችልበት ሁኔታ የክልሉን ኢኮኖሚ "በፓርቲ ኩባንያዎች" አማካይነት ጠቅልሎ የሚቆጣጠር፣ የልማቱንም የእድገቱንም አቅጣጫ ለራሱ ጥቅም እየቀየሰ የሚንቀሳቀስ አጥፊና አደገኛ ክሊክ ነው። ሆኖም የዚኽ ኦሊጋርሺ አጥፊነትና

እሱንም የመዋጋቱ ጉዳይ አስፈላጊነት እንዳለ ሆኖ አንድ መገንዘብ ያለብን ሌላ ሃቅ አለ፡፡ የለየለት ዘረኝነትና ጥላቻ ካልተጠናወተን በስተቀር ከሌሎቹ የአገራችን ዴሞክራቶች የተለየ ህልምም ሆነ ራእይ የሌላቸው ዴሞክራትና አገር-ወዳድ የትግራይ ተወላጆች እንዳሉም መካድ ጨርሶ የሚቻል አይደለም፡፡

እነዚኽ ወገኖቻችን በትግሉ ውስጥ የሚያደርጉት ተሳትፎ በተለይ የሕወሓት መሪዎች የትግራይን ሕዝብ በጉያቸው ለማስገባት የሚያደርጉትን መሰሪ እንቅስቃሴ ለማክሸፍ የትግራይ ሕዝብና ሌሎቹ የአገራችን ብሔር/ብሔረሰቦች እንዲዘፈቁበት የሚፈልገውን የጥላቻና የብሔማ ፍራቻ አዙሪት ለመስበር ወሳኝ የሆነ ሚና ሊጫወት የሚችል ተሳትፎ ነው፡፡ የሕወሓት መሪዎች ፀረ-ኢትዮጵያ ወንጀል በትግራይ ብሔር ስም የሚፈጸም በመሆኑ እኛ የለም የትግራይን ሕዝብ አትወክሉም እያልን የምናስተጋባውን ሃቅ የትግራይ ዴሞክራቶች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው "የለም አትዋሽ፣ አትወክለንም" እያሉ ቢያስተጋቡት ይበልጥ ፖለቲካዊና ሥነ-ልቡናዊ ትርጉም እንደሚኖረው ምንም የሚያጠራጥር አይደለም፡፡ የሕወሓት መሪዎች እንዲህ ዓይነቱ የጎላ ተሳትፎ በጥላቻና በፍራቻ ላይ የገነቡትን ስትራቴጂ እንደ እምቧይ ካብ የሚያፈራርስ በመሆኑ ከጦር ይፈሩታል፡፡ በመሆኑም የትግራይን ዴሞክራቶች የቀረነውን ከትግራይ ያልተወለድነውን ዜጎች በሚያዩበት ዓይን አይደለም የሚመለከቷቸው፡፡ ለሕወሓት መሪዎች እኛ ተራ ተቃዋሚዎች ነን፡፡ እነሱ (የትግራይ ዴሞክራቶች) ግን "ከሃዲዎች" ናቸው፡፡ በዚኽ መልክ መፈረጁ በራሳቸው ላይ ብቻ ሣይሆን ዘመድ አዝማድና ወዳጅ ላይ ሳይቀር የሚያመጣው ችግር በቀላሉ የሚታይ ባይሆንም ይኽንን ተጨባጭ ሁኔታ አጢኖና ከነሱ ጋር የሰከነና ቀጣይነት ያለው ውይይት አካሂዶ አንድ የጋራ ስምምነት ላይ መድረስ አስፈላጊ ይመስለኛል፡፡ ይኽንን ካልቻልንና እኛ ከየትኛውም የአገሪቱ ብሔር/ብሔረሰብ የተሰባሰብን የኢትዮጵያ ዴሞክራቶች በጋራ አቋም የጋራ ትግል የምናካሂድበት ዘዴ ካላበጀን ከየብሔማቋ የተውጣጡ አክራሪዎች ጭቁኖችን በጎሣና በሐይማኖት እያናከሱ የዚኽን ሰማዕት ሕዝብ የሰቆቃ ዘመን የሚያራዝሙበትን ሁኔታ እያመቻቹላቸው እንደሆነ መገንዘብ ይኖርብናል፡፡

እኛ ዴሞክራቶች ከአለው ተጨባጭ ሁኔታና በየብሔሩ ያሉ በዚኽ ጥያቄ ለመነገድ ከሚሹ ኃይሎች ጋር በምናደርገው ትግል ወንድማማችነትን፣ አንድነትን አንግበን በሰከነና መርኅ በተከተለ ሁኔታ በጋራ ልንታገልላቸው ካልተነሳን፤ ቀጣዩና አይቀሬው ትርምስ የዚኽ ወይም የዚያ ብሔር ሳይባል ለዴሞክራቶች በሙሉ አስቸጋሪ የሚሆንበትና ከየብሔሩ የተውጣጡ አክራሪዎች ደግሞ ከነጥፋት አጀንዳቸው መኻል መድረኩን ይዘው አገራችንን የሚያደሙበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

በሕወሓት መሪዎች የትግራይ ሕዝብ ሌሎቹን የኢትዮጵያ ብሔር/ብሔረሰቦች የጎልውናው ጠር አድርጎ እያየ እንዲጠላቸውና እንዲፈራቸው የሚደረገው ጥረት አይቀሬ ውጤት በሁሉም ብሔሮች ውስጥ ላሉና "እኛም የብሔራችን ብቸኛ ተወካይ ነን" ለሚሉና ብሔራቸው የትግራይን ሕዝብ እንደ ደመኛ ጠላት አድርጎ እንዲቆጥር ያላሰለሰ ጥረት ለሚያደርጉ ሌሎች አክራሪዎች በሩን በርግዶ መክፈት ነው፡፡

የእንዲህ ዓይነቱ አካሄድ ችግር በሁሉም ብሔሮች ውስጥ ያሉ ዴሞክራቶች ለአንድነት፣ ለሕዝብ ወንድማማችነት ብሎም ደግሞ ዞሮ ዞሮ ለዴሞክራሲ የሚደረገውን ትግል የአቀበት ጉዞ የማድረግ ችግር ብቻ አይደለም፡፡ ሜዳውን ለነዚኽ አክራሪ ኃይሎች ከተውንና አፀፋ ስትራቴጂ አውጥተን ካልተንቀሳቀስን ስሜቶች መረን ለቀው የሚስፋፉበትና የቦዝንያና የሩዋንዳ ዓይነት አስከፊ ሁኔታ የሚከሰትበት አደጋ እንዳለ ግንዛቤ መጨበጥ ይኖርብናል፡፡

ከባዱን፣ ውስብስቡና ሕዝባችንን ቀስቅሶና ይዞ የመንቀሳቀስ ነገር በሕወሓት የሽብርና የአፈና አገዛዝ ሥር እጅግ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ከዚኽ ተነስተን ሲያዩት ቀላል ግን ደግሞ አደገኛ የሆነውን የነዚኽን የጥፋት ኃይሎች አጥፊና መርዘኛ ስትራቴጂ የሚያግዝና ወንድም/እህት የሆነው የትግራይ ሕዝብ “ለካ እውነታቸውን ኖሯል” ወደሚል ድምዳሜ ደርሶ ከጋራው ትግል ጎራ ይልቅ ወደ ፀረ-ሕዝቦቹ ጉያ እንዲገባ የሚያደርግ ቅስቀሳ የትም አያደርርሰንም፡፡ ማንም ዴሞክራት፣ ማንም ኢትዮጵያዊ አገር-ወዳድ ብሎም ማንም የኢትዮጵያ ብሔር/ብሔረሰብ ከዚኽ የሚያገኘው ምንም ገንቢ ነገር የለምና፡፡

የተያዘው ተጋድሎ ኅብረ-ብሔር የሆኑ ጥቂት ፀረ-ሕዝቦች የተከሉብንን ሙሰኛና ግፈኛ ሥርዓት እኛም እንደ እነሱ ብሔርና ጎጥ ሳንል በአንድነት ቆመን፣ ብሔርና ጎጥ ሳንል ሕዝባችንን በጋራ አንቀሳቅሰን ዴሞክራሲያዊት፣ ፍትኃዊትና አንዲት በዓለም ሕዝቦች ሸንጎ አኩሪ ታሪኳ የሚሰጣትን ቦታ የምትይዝ አገር የመመሥረት ተጋድሎ ነው፡፡ ይኽንን ያኽል ሰፊና ታሪካዊ ተልዕኮ እያለብን በፀረ-ሕዝቡ ሰፈር ይኽኛው አናሳ ክሊክ ከዚያኛው ፀረ-ሕዝብ ስብስብ የበለጠ ቦታ ይዟል፣ ይኽንን ብሔር “እወክላለሁ” እያለ የሚቀጥፈው ቡድን ያኛውን ብሔር “እወክላለሁ” ከሚለው ዋሾ ይበልጥ ድርሻ ተሰጥቶታል የሚል ንትርክ ውስጥ መግባት የለብንም፡፡ ነገ በሆነ ተአምር ኢሕአዴግ “ዴሞክራሲያዊ” አሠራር ተከትሎ በሠራዊቱም ሆነ በጠቅላላው በመንግሥቱ መዋቅር ውስጥ ያሉትን ቁልፍ ቦታዎች እነዚኽ ጥቂቶች ይበልጥ “ፍትኃዊ” በሆነ ዘዴ ሊቀራመቱ ይችላሉ፡፡ በዚኽ መልክ የየብሔሩ ተወካይ ተብየ “ድርሻ” ይበልጥ ተመጣጣኝ ቢሆን፣ ሌላው ቀርቶ “ትግራዊው” መለዝ ዜናዊ ነገ ጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ለሆነ የአማራ ወይም የኦሮሞ ተወላጅ ቢለቅ ለኛም ለኢትዮጵያም ሕዝብ የሚያስገኘው ቅንጣት ነገር የለውም፡፡ ለዚኽ ነው ይኽን ጽሑፍ “የሕወሓት መሪዎችን ጠበቅ” ከማለት ይልቅ የተያዘው ትግል ምንም እንኳን በአመዛኙ ገፅታው ከነዚኽ የጥፋት ኃይሎች ጋር ቢሆንም ከነሱም ዘልቆ በጥቅም የተሳሰሩ ጥቂቶች በታጎሩበት ኅብረ-ብሔር ስብስብ ላይ ማተኮር ይገባዋል በሚል መንፈስ “የሕወሓት/ኢሕአዴግን መሪዎች ጠበቅ” የሚል ርእስ ልሰጠው የፈለኩት፡፡

ዶ/ር ነገደ ጎበዜ
ሰኔ፤ 2001 ዓ/ም

--------- // --------

## ዜና

### *የሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ “ፀረ-ሽብር ሕግ” ሕገ-አራዊት ነው ተባለ፤.....*

ባለፈው ሰሞን በሚንስትሮች ምክር ቤት “ፀድቆ“ ለአገዛዙ ተወካዮች ም/ቤት (ፓርላማ) የተላከው “ፀረ-ሽብር” ረቂቅ ሕግ በአገዛዙ ላይ ተቃውሞ እንዳይነሣ ለማድረግ ተቃዋሚዎችን ነጥሎ የመምቻ፣ ዜጎች ለመብታቸው መከበር የሚያደርጉትን የዴሞክራሲ ትግል ለመደፍጠጥና ነፃነታቸውን ለማፈን የሚደረግ ፀረ-ዴሞክራሲና የሕግ ልዕልናን በእጅጉ የሚፃረር፣ ለሰው ልጅ የማይመጥን 'ሕገ-አራዊት' ነው ሲሉ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተቃውሞአቸውን አሰሙ፡፡
በተያያዘ ዜናም ዓለም-አቀፉ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች (ሂውማን ራይትስ ዋች) የፀረ-ሽብር ረቂቅ ሕግ መሠረታዊ የሆኑ የመናገርና በሰላም የመሰብሰብ መብቶችን ይጥሳል ሲል ስጋቱን ገልጿል፡፡ በዚኹ ይፋ በሆነ የተቋሙ ዘገባ መሠረትም የፖለቲካ ንግግሮችንና ሰላማዊ ተቃውሞን በሽብር በመፈረጅ የሚቀጣ፣ ፀድቆ ሕግ ከሆነም ኢ-ፍትኃዊ የፍርድ ሂደትን የሚያበረታታ እንደሆነ አስታውቋል፡፡

### *ሕወሓት/ኢሕአዴግ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ላይ ያለው ጥላቻ አገረሸበት፤ ....*

የኢትዮጵያውያን የነፃነት፣ የሉዓላዊ-ነትና የአንድነት ምልክት የሆነችው አረንጓዴ-ብጫ-ቀይ ብሔራዊ ዓርማችንን (ሰንደቅ ዓላማ) መጠቀም የሚከለክልና የሚቀጣ ሕግ እየተዘጋጀ መሆኑን ሪፖርተር የተባለው ለአገዛዙ ቅርበት ያለው ጋዜጣ አስታወቀ። ይኸው ሕግ (ብይን) ተግባራዊ መሆን ሲጀምር በሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ዘመን በሰንደቅ ዓላማው መኻል የተለጠፈ ምልክት የሌለበትን ማውለብለብ የሚያስቀጣ መሆኑንና እንዲሁም በሕዝብ በዓላትም ሆነ በተለያዩ ዝግጅቶች ላይ መጠቀም እንደማይቻል የሚከለክል ረቂቅ ሕግ ነው ተብሏል።

### *ይቻላል ተደነቀች፤.....*

በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት የሕዝብ ግንኙነትና ማስታወቂያ ክፍል የምትዘጋጀውና የኅብረቱ ልሳን የሆነችው 'ይቻላል' ቅጽ አንድ ቁጥር አንድ በይዘቱና የግንቦት ቅልበሳ መዘዙንና የወደፊት አቅጣጫ አመላካች የሆነው ትንተና እንዲሁም ለውጥ ለማምጣት 'ይቻላል፣ መቻልም አለበት' የሚለው ተስፋንና ቁርጠኝነትን አብሳሪ የሆነው አቀራረብ አበረታች ሆኖ እንዳገኙት ከርካታ ወገኖች ለዝግጅት ክፍሉ በተላኩ 'በርቱ፣ ግፉበት' የሚሉ መልዕክቶቻቸው መረዳት ተችሏል።
በዚኽ አጋጣሚ መልዕክቶቻቸውን ላስተላለፉልን ወገኖቻችን ምስጋና ስናቀርብ ማንኛውንም አስተያየት፣ ጥያቄም ሆነ ትችት በአድራሻዎቻችን ቢላኩ በደስታ እንደምናስተናግድ ስንገልጽ 'ይቻላል' እስከ ሕዝባዊ ድል እውን መሆንና መረጋገጥ ትቀጥላለች.....

---------- // ---------

## ኅብረቱ ምን ብሎ ነበር?

*ይቻላል በዚኽ አምድ ሥር ቀደም ሲል ኅብረቱ በአንዳንድ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ የወሰዳቸውን አቋሞችና ይዘታቸው አሁንም ለቀጣዩ ትግል ጠቃሚ ይሆናል ብሎ ያመነባቸውን ለአንባቢ የሚያቀርብበት ክፍል ነው።*

## ሕዝባዊ ሰላማዊ ትግል ስንል፤

### ሽብርና አምባ-ገነንን ተቋቁሞ ለአዲስ ሥርዓት ግንባታ መጣኝ ትግል፤

የኢሕአዴግ መሪዎች የተያያዙት የቅልበሳ ሂደት አንዱ ገፅታው ግንቦትን ያስቻሉትን የፖለቲካ፣ የአስተሳሰብ፣ የተቋማት ግኝቶች እንዳልነበሩ አድርገው በማውደም በአፈናና በሽብር መጨረሻው ለማይታይ ረጅም ወቅት በኅብረተሰባችን የሽግግር ክፍተት የመፍጠር ሂደት ነው። እነዚኽ ፀረ-ሕዝብ ኃይሎች በሕዝባችን ተጋድሎ ከጥፋት ሂደታቸው እንዲያፈገፍጉ ከመገደዳቸው በፊት ከእንግዲህ የሕግ የበላይነት፣ የዳኝነት ነፃነት፣ ተጠያቂነት፣ የፕረስ ነፃነት፣ በነፃ የመደራጀት መብት፣ ነፃ ምርጫ፣ ወዘተ.. የሚሉ ከባድ ከባድ እሴቶች ቀርቶ በቅድመ-ግንቦት ወቅት የነበሩት የዴሞክራሲ ፍንጮች እንኳ እውን የሚሆኑበት ምንም ዓይነት ተአምር አይኖርም። ከዚኽ አንፃር የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ደግሞ ደጋግሞ ያስተጋባው ጥሪ **ሁላችንም ለግንቦት ድሎች ብለን እንነሳ የሚል** ነው። ይኽ ማለት ግንቦትን ያስቻሉትና ዛሬ ደብዛቸው የጠፋው የዴሞክራሲ መብት ፍንጮች መልሰው እውን እንዲሆኑ መታገል ብቻ አይደለም። የኢሕአዴግ መሪዎች ዛሬ ባሉበት የኪሣራና በሕዝብ የመተፋት ደረጃ ባልተሟላ ሁኔታ እውን የነበሩ ቢሆኑም እነዚህ መብቶች እርግጥ ሕዝባችን የፈለገውን እንዲመርጥ አስችለውት ነበር። ነገር ግን ድምፁን ለማስከበር ብቁ እንዳልነበሩ የዚያኑ ያኽል ግልፅ ይመስለናል። ለዚኽ ነው **"ለግንቦት ድሎች"** መታገል ባልን ቁጥር "በዚያው

ሂደት በነሱው ላይ መገንባት" እያልን ትግላችን መሥመር የሳተው የዴሞክራሲ ሂደቱ (ዴሞክራታይዜሽን) መልሶ በእግሩ እንዲቆምና ሂደቱ ቀጥሎ በአገራችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሰፍኖ የዚኽ ሁሉ መቋጠሪያ በሆነው ነፃና ርቱዓዊ ምርጫ እንዲቋጭ ሳያቋርጥ መቀጠል ያለበት ታሪካዊ ተጋድሎ ነው የምንለው::

ለዚኽ ነው ከእንግዲህ ይኽ ፀረ-ሕዝብ ሥርዓት በሕዝብ ኃይል ተገዶ ዴሞክራሲ ከመስፈኑ በፊትና ምርጫም ከተባለ ነፃ የሆነ የምርጫ አስፈጻሚ አካል (ቦርድ) በሌለበት ሁኔታ ስለ ምርጫ ማውራት በሕዝብ ትግል ማሾፍ የሚሆነው:: ለዚኽም ነው ከእንግዲህ ትግላችን እንደ ቅድመ-ግንቦቱ ወቅት በምርጫ ዙሪያ ሳይሆን ሕዝባዊ የትግል ማዕበል ለመቀስቀስና ለመምራት መሆን ይኖርበታል የምንለው:: ስለሆነም የዴሞክራሲ ፍንጮች በነበሩበት ሁኔታ እንኳን አልጋ-በአልጋ ያልነበረው የዚኽ ሰማዕት ሕዝብ ትግል ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ውስብስብ፣ በጣም ከባድና የበለጠ መስዋዕትነትን የሚጠይቅ ሂደት ይሆናል የምንለው:: ለዚኽም ሁሉ ነው በዚኽ ታሪካዊ ተጋድሎ "እንኖርበታለን" ብለን በሕዝባችን ፊት ቃል ከገባንና ይኽንን ቃላችንን ከምር ከወሰድን አይቀር ለተቀበልነው ተልዕኮና ላለንበት አዲስ የትግል ምእራፍ በሚመጥን ሁኔታ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረትን አወቃቀር አባል ድርጅቶች ከየድርጅች ነፃነታችን ቀንሰን ለጋራው ትግል በሚያስረክብና የሥራ ቅልጥፍናን የበለጠ በሚያመቻች መልክ ለማሻሻል የመረጥነውና የጥምረት አደረጃጀትንና አወቃቀርን የመረጥነው::

ይኽንን የዴሞክራሲ ሂደት (ዴሞክራታይዜሽን) ትግል ከግቡ ማድረስ ከፈለግን የግባችን ትልም (የስትራቴጂ-ያችን) ሁሉ መነሻ ግንቦት የሚሊዮኖች ድል እንደነበረ ሁሉ እነዚኽን ድሎች አስከብሮ ወደፊት ለመራመድ በግንቦት የዴሞክራሲ፣ የፍትኅ፣ የሕዝብ ወንድማማችነትና የአገር አንድነት እሴቶች ዙሪያ ሁሉም በአንድ አቅጣጫ የሚገፋበት የሚሊዮኖች ትግል ያስፈልጋል የሚለው እምነት መሆን ይኖርበታል:: በኛ ግምት ዛሬ ኅብረተሰባችን ለሚገኝበት አስከፊ ሁኔታና ለትግሉ አደገኛ መዝረክረክ መሠረታዊ ምክንያት የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ሆን ብለው እኛ ደግሞ በእይታ ጉድለትም ይሁን በሌሎች ምክንያቶች ግንቦት ላይ **የትግሉም የድሉም ዋና ባለቤት የነበረው ሕዝባችን ከፖለቲካው መድረክ እንዲገለል ማድረጋችን** ይመስለናል:: ዛሬ ከምንገኝበት አጣብቂኝ ለመውጣት ከፈለግን የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎችን በአሥራ-አራት ዓመታት የግፍ አገዛዛቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ተከላካይነት ኅብረተሰባችንን ደግሞ ወደማያወላዳ የፖለቲካ የበላይነት ያሸጋገረውን ይኽንን ሕዝባዊ ተሳትፎ **መልሶ እውን ማድረግና ሕዝባችን መልሶ የትግሉ ባለቤት መሆኑን ማረጋገጥ** የትግላችን ትልም (የስትራቴጂ-ያችን) የማዕዘን ድንጋይ አድርገን መንቀሳቀስ ይኖርብናል::

ዋናው የትግላችን ዓላማ ግንቦት ላይ እኛን ባኮራ፣ ዓለምን ባስደነቀ፣ የሕወሓት/ ኢሕአዴግ መሪዎችን ብርክ ባስያዘ ወኔ ሕዝባችን እንደ አንድ ሰው ተንቀሳቅሶ ዴሞክራሲ በአፋኝ አገዛዝ ላይ፣ የሰላማዊ ለውጥ አሳብ በአመፅ ፖለቲካ ላይ፣ የሕዝብ ወንድማማችነትና
የአገር አንድነት እሴት በአናክሰሀ-ግዛ ርኩስ ፖለቲካ ላይ ድልን ለማጎናፀፍ ያስቻለውን ሕዝባዊ የትግል ማዕበል መልሶ በመቀስቀስ የበጎ አዙሪት ሂደት የመክፈት ዓላማ ነው:: ሆኖም ትኩረታችን በግንቦት እሴቶች ዙሪያ የግንቦት ኃይሎችን በሙሉ አንቀሳቅሰን እንዴት ያኔ የተጎናፀፍነውን የማያጠራጥር የፖለቲካ የበላይነት መልሰን እንያዝ? የሚለው ጥያቄ ላይ መሆን ሲገባው ዛሬ በተቃዋሚው ጎራ ለምን እንታገል? በሚለው ጥያቄ ላይ ሳይሆን እንዴት እንታገል? በሚለው ነጥብ ላይ ልዩነቶች ሲከሰቱ እናያለን:: ለኛ በመካሄድ ላይ ያለው ክርክር "ሰላማዊ ትግል ወይስ የትጥቅ ትግል" በሚለው ጥያቄ ዙሪያ

የታጠረ ቁንፅል ክርክር ይመስለናል።

በዚኽ በትግል ስልት ጉዳይ አንድ በጣም ግልፅ መሆን ያለበት ቁም-ነገር አለ። ዛሬ በአገራችን ዓላማውን ለማራመድ ከአመፅ፣ ከሽብርና ከሕገ-ወጥነት ሌላ ምንም ምርጫ የሌለው አንድ ኃይል ቢኖር ሕወሓት/ኢሕአዴግ ብቻ ነው። የዚያኑ ያኽል ደግሞ ሕዝባዊ የግንቦት ኃይሎች በግንቦት እሴቶች ዙሪያ በአንድ አቅጣጫ ለመንቀሳቀስ እስከተስማሙና የሕዝባችንን የትግሉ ማዕከልነት እስከተቀበሉ ድረስ የትግል ስልት ምርጫው ምንም ወሰን የሌለው፣ ትግላቸውም በምንም ቀኖናዊነት የማይታጠር ዘርፈ-ብዙና ሁሉን አቅጣጫ ያየና የዳሰሰ እንደሚሆን ግልፅ ነው። በሕዝባችን የትግሉ ማዕከልነት ላይ ስምምነት ካለና ለዚኽና ወደዚኽ ከተሠራ ማንም ይሁን ማን ያመቸኛል በሚለው ስልት ቢሰማራ ይኽ የልዩነትና የክፍፍል ምንጭ መሆን አይኖርበትም። የሕዝባችንን አጀንዳ እስካነገበ ድረስ ማንም ኃይል "አምንበታለሁ፣ ይቻላል" በሚለው ሕጋዊ ሆነ ሕገ-ወጥ፣ ይፋ ሆነ ኅቡእ፣ ሰላማዊ ሆነ የትጥቅ ትግል መስክ ሊሰማራ የማይችልበት ምንም ምክንያት አይኖርም።

ቀስ በቀስ በግንቦት እሴቶች ዙሪያ ሕዝባዊ የትግል ማዕበል የመፍጠር ዓላማ የሌለው እስከሆነ ድረስ "ሰላማዊ" የሚባለው ትግል የጥቂት ግንባር-ቀደም ኃይሎች ግርግር ከመሆን አልፎ የምንፈልገውን የነፃነት ፈር አያስይዘንም። የግንቦት ኃይሎች የግንቦትን እሴቶች አንግበውና ሕዝባችን የማያጠራጥር የፖለቲካ የበላይነትን መልሶ ጨብጦ ከዳር-እስከ-ዳር በማይንቀሳቀስበት ሁኔታ የተለያዩ ኃይሎች አንዳንዴም የግንቦትን እሴቶች በሚቃረኑ የተሰበጣጠሩ ወገናዊ አጀንዳዎች እናካሂዳለን የሚሏቸው የትጥቅ ትግሎችም የጋራችን ከሆነችው አገርና ከሕዝባችን ዘለቄታዊ ጥቅሞች አንፃር ሲታይ የትም የሚያደርሱ አይደሉም። ይኽ ማለት ዛሬ አገራችንን በመቆጣጠር ላይ ካሉት ጦር-ጠማኘሽ ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች አንፃር ትጥቅ አንስቶ መፋለም አያስፈልግም ማለት እንዳልሆነ ግልፅ ነው። ሆኖም ከወሳኙ ሕዝባዊ የአንድነትና የጋራ ተጋድሎ አንፃር እነዚኽ ኃይሎች በግንቦት እሴቶች ዙሪያ ሕዝባችን በሚሊዮን እየተቆጠረ ለሚያካሂደው ትግል አጋዥ ሆነው ራሳቸውንም የዚኽ ታሪካዊ ተጋድሎ"የታጠቀ ክንፍ" አድርገው ካልተንቀሳቀሱና አልፈው ተርፈው ደግሞ ይኽንን ሕዝባዊ ትግል "እንተካለን" ብለው የሚግደረደሩ ከሆነ የትም እንደማይደርሱ በጣም ግልፅ መሆን ይኖርበታል።

*ይቀጥላል......*

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)

ሰኔ፣ ፪ ሽህ ፩ ዓ/ም (June, 2009)